# ኢትዮጵያ በጸጥታ ጥበቃው ምክር ቤት መድረክ

## ኢዛና ዘ መንፈስ 09-23-17

ኢትዮጵያ መላውን የአፍሪካ ሀገራት ወክላ ለፀጥታው ምክር ቤት ተለዋጭ አባልነት ከተመረጠች እነሆ አንድ ዓመት ሊሞላት ነው፡፡ በተለይም ደግሞ አሁን ላይ ዓለም አቀፋዊውን የፀጥታ ምክር ቤት በፕሬዚዳንትነት እየመራች የምትገኘው ሀገራችን ኢትዮጵያ ለአንድ ዓመት የሚቆየውን የተለዋጭ አባልነት ሚናዋን ከመወጣት አኳያ ምን ያህል ጥረት እንዳሳየች መገምገም ተገቢ ይመስለኛል፡፡ ስለሆነም የዚህ መጣጥፍ ዓላማ ኢትዮጵያ በፀጥታው ምክር ቤት ተለዋጭ አባል ሆና ከተመረጠችበት ጊዜ ጀምሮ እንደብቸኛ አፍሪካዊት ሀገር ለአህጉሪቱ ችግሮች ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ተገቢ ትኩረት እንዲሰጥ በማድረግ ረገድ ምን ያህል ርቀት ተጉዛለች? እውን አፍሪካውያን ህዝቦች የጣሉበትን እምነት የሚመጥን አዎንታዊ ተጽዕኖ ለማሳደር የቻለ ዲፕሎማሲያዊ ሚና በመጫወት ላይ ናትን? የሚል ጥያቄ ማንሳትና ሚዛናዊ ምላሽ ለመስጠት መሞከር ተገቢ መስሎ ይሰማኛል፡፡

እናም እንደኔ እንደኔ ሀገራችን ኢትዮጵያ አፍሪካን እንደ አህጉር ወክላ በዓለም አቀፋዊው የፀጥታ ጥበቃ ምክር ቤት ውስጥ ተለዋጭ አባል ስትሆን፤ በተለይም ለአፍሪካ ሀገራት ጥያቄ ደረጃ በደረጃ ምላሽ የመስጠት ዓለም አቀፋዊ ፍቃደኝነትን የሚያስከትል አዎንታዊ ተጽዕኖ የማሳደር ትርጉም ያለው ሚና መጫወት እንደሚኖርባት አበክራ ትገነዘብ እንደነበር ነው ሊሰመርበት የሚገባው ቁልፍ ነጥብ የሚል እምነት አለኝ፡፡ ምክንያቱም ሰሞኑን በአሜሪካ ኒውዮርክ የተካሄደው የተባበሩት መንግስታት መደበኛ ስብሰባ ላይ የተገኙት የኢፌድሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር አቶ ኃ/ማርያም ደሳለኝ፤ የወቅቱ የፀጥታ ጥበቃው ምክር ቤት ፕሬዚዳንት የሆነችውን ሀገራችንን ወክለው በመሩት የዓለም መሪዎች የውይይት መድረክ በአጽንኦት ያስገነዘቡት መሰረታዊ ጉዳይ፤ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ለአፍሪካ ችግሮች መቀረፍ መጫወት የሚጠበቅበትን ገንቢ ሚና፤ በመጫወት ረገድ ከተራ ቃል መግባት የዘለለ ተግባራዊ ምላሽ ሊሰጥ እንዳልቻለና ግን ደግሞ መስጠት እንደሚኖርበት የሚያስገነዝብ ጠቃሚ ሃሳብ ያቀረቡበትን አግባብ ማጤን ይቻላልና ነው፡፡

ከዚህ የተነሳም፤ ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ስር የሚገኘውን የፀጥታው ጥበቃ ምክር ቤትን ለአንድ ወር በፕሬዚዳንትነት የመምራት ስልጣን ተሰጥቷት የቆየች ሀገር እንደመሆኗ መጠን፤ በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ የተገኘውን አዎንታዊ ተጽእኖ የማሳደር ዕድል ሁሉ፤ በአግባቡ ለመጠቀም ያለመ ጥረት እንዳሳየች ነው መረጃዎች የሚያመለክቱት፡፡ ለአብነት ያህልም፤ አሁንም የመላው ሰብዓዊ ፍጡር ብርቱ የደህንነት ስጋት እንደሆነ የሚገኘውን ዓለም አቀፍ የሽብርተኝነት እንቅስቃሴ በመታገል ረገድ፤ የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ እየተደረገ ያለውን የተናጠል ጥረት፤ እንዴት ወደተቀናጀ አህጉራዊ የትብብር ማዕቀፍ ማሳደግና አደጋውን በተሻለ መልኩ መቀልበስ እንደሚቻል የሚያመለክት አዲስ ዓይነት የፀረ ሽብርተኝነት ስትራቴጂ ነድፋ ለመንግስታቱ ድርጅት ሰባ ሁለተኛው ጠቅላላ ስብሰባ ያቀረበችው ኢትዮጵያ በጉባኤተኛው ዘንድ የላቀ አድናቆት እንደተቸራት መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ይልቁንም ደግሞ ኢትዮጵያ ከአንድ ዓመት በፊት የፀጥታው ምክር ቤት ተለዋጭ አባል ሆና ስትመረጥ ቃል በገባችው መሰረት፤ ለዓለም አቀፍ የሰላም ማስከበር ተልዕኮ የሚሰማሩት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ወታደሮች ስኬታማ ተግባር ለመከወን እንዲችሉ የሚረዳ የማሻሻያ ሰነድ አዘጋጅታ ከማቅረቧም ባሻገር ሰነዱ በከፍተኛ የአባል ሀገራት ድጋፍ ጸድቆላታል፡፡ በዚህ መሰረትም 15 ሀገራትን በአባልነት ያቀፈው የፀጥታ ጥበቃው ምክር ቤት ኢትዮጵያ አዘጋጅታ ያቀረበችውን የማሻሻያ ሰነድ ያለምንም ተቃውሞ (በሙሉ ድምጽ) ሊያጸድቀው መቻሉን ነው የታመኑ የመረጃ ምንጮች ያመለከቱት፡፡ በአጠቃላይ ኢትዮጵያ፤ አሁን በተካሄደው የመንግስታቱ ድርጅት 72ኛ መደበኛ ጉባኤ ላይ የስብሰባውን መድረክ ከመምራት ጀምሮ ትርጉም ያለው አዎንታዊ ተጽእኖ የፈጠረችበት ነው ሊባል የሚችል ንቁ ተሳትፎ አሳይታለች፡፡

እንዲያውም አንዳንድ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ወገኖች እንደሚሉት ከሆነማ፤ ላለፈው አንድ ዓመት የፀጥታ ጥበቃው ምክር ቤት ተለዋጭ አባል ሀገር ሆና ስትሰራ የቆየችው ኢትዮጵያ በሰባ ሁለተኛው የመንግስታቱ ድርጅት መደበኛ ስብሰባ ላይ ያቀረበችው የፀረ ሽብርተኝነት አህጉር አቀፍ የትግል ስትራቴጂካዊ ሰነድ፤ በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ ሌላ ተጨማሪ አድናቆትንና ተቀባይነትን ሊያተርፍላት ይችላል፡፡ ይህን አስተያየት ሲሰጡ የሚደመጡት ታዛቢዎች መከራከሪያቸውን አሳማኝ ለማድረግ ሲሉ የሚያነሱት ምክንያትም ደግሞ፤ በተለይም ዓለም አቀፍ ሰላም የማስከበር ተልእኮ ላይ በመሰማራትና ውጤታማ ተግባር በመከወን ረገድ የተመሰገነ መልካም ስም ካላቸው ጥቂት ሀገራት መካከል አንዷ የሆነችው ኢትዮጵያ፤ ሽብርተኝነትን ከመታገል አኳያም ለሌላው ዓለም የሚተርፍ ጠቃሚ ልምድ አዳብራለች የሚል ነው፡፡

ይህ የታዛቢዎቹ ወገኖች አስተያየት፤ በእርግጥም ለዛሬዋ ኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት የሚገባቸውን ቦታ የሚሰጥ ሚዛናዊ ሃሳብ እንጂ ተራ ለራስ ሀገር የማድላት ውዳሴ ከንቱ እንዳልሆነም ነው እኔ በግሌ የማምነው፡፡ እንዴት ቢባል ደግሞ፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ የምትገኝበት ይህም የምስራቅ አፍሪካ ቀጣና ለዓለም አቀፋዊ የሽብርተኝነት እንቅስቃሴ ተጋላጭ ተደርገው ከሚወሰዱ አካባቢዎች አንዱ ሆኖ ሳለ፤ ግን ደግሞ ከሁሉም ጎረቤት ሀገራት በተሻለ አንፃራዊ ሰላምና መረጋጋት ውስጥ የምትኖር ስለመሆኗ ይታመናልና ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር ኢትዮጵያ ሌሎች አፍሪካውያን ወንድም ህዝቦችን በገጠማቸው የዕርስ በርስ ግጭት ምክንያት ጎራ ለይተው ከመተላለቅ ለመታደግ ስትል በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወታደሮቿን ወደ ተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት እያሰማራች ዓለም አቀፋዊ አድናቆት ያተረፈችበትን ውጤታማ የሰላም ማስከበር ተልዕኮ በማስፈፀም የምትታወቅም ጭምር የመሆኗ ጉዳይ ፀሐይ የሞቀው ጥሬ ሀቅ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ እናም በሰሞነኛው የተ.መ.ድ.መደበኛ ጉባኤ ላይ ከተመከረባቸው የወቅቱ ዓለም አቀፋዊ አንገብጋቢ ችግሮች መካከል አንዱ ስለነበረው በተለያዩ ሀገራት ውስጥ ለሰላም ማስከበር ተልዕኮ እየተሰማሩ በአገሬው ሴቶች ላይ የአስገድዶ መድፈር ፀያፍ ተግባር የሚፈጽሙ ወታደሮችን በሕግ ፊት ቀርበው እንደጥፋታቸው ልክ እንዲጠየቁ ስለማድረግ ጉዳይ በተነሳ ነጥብ ዙሪያ አስተያየታቸውን ሲሰጡ የተደመጡት የጉባኤው ተሳታፊዎች ለኢትዮጵያ ሰላም አስከባሪ ወታደሮች ህዝባዊነትና አርአያነት ያለው ዲሲፐሊን አድናቆታቸውን ሳይገልጹ አላለፉም፡፡

ይሄን በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ስር ለሚደረግ ዓለም አቀፋዊ ሰላም የማስከበር ክቡር ተልዕኮ ተሰማርተው ሳለ፤ እጅግ በጣም የዘቀጠና ኢ ሞራላዊ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ስለሚፈጽሙ ምግባረ ብልሹ ወታደሮች ጉዳይ የሚያወሳ አጀንዳ ለውይይት ያቀረበችውም፤ የወቅቱ የፀጥታው ጥበቃ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት የሆነችው ሀገረ-ኢትዮጵያ ናት፡፡ እናም ሀገሬ ድርጊቱ የሰላምና መረጋጋት እጦት ግንባር ቀደም ሰለባ የመሆን ከፉ ዕጣ የገጠማቸውን አቅመ-ቢስ የአፍሪካ ሀገራት ሴቶች ከማንኛውም ዓይነት የኃይል ጥቃት የመታደግ ክቡር ዓላማ ይዞ ከሚሰማራው የተ.መ.ድ. ሰላም አስከባሪ ሰራዊት መካከል አንዳንድ እንሰሳዊ ባህሪ የተጠናወታቸው ወታደሮች ይፈጽማሉ የተባለው እጅግ አስነዋሪ የሰብዓዊ ሙብት ጥሰት ጉዳይ በቸልታ መታለፍ እንደሌለበት ነው አጥብቃ ያሳሰበችው፡፡

ይህ ማለትም ደግሞ ኢትዮጵያ መላውን የአፍሪካ ሀገራት ወክላ በተመረጠችበት የፀጥታ ጥበቃው ምክር ቤት ተለዋጭ አባልነት ለአንድ ዓመት ያህል ስትቆይ በተለይም ለአህጉራችን ህዝቦች አሳሳቢ የጋራ ችግሮች ዘለቄታዊ መፍትሔ ስለመስጠት አስፈላጊነት ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በቅጡ እንዲረዳ በማድረግ ረገድ ያላሰለሰ ጥረት ከማሳየት የቦዘነችበት አጋጣሚ እንዳልነበርና የማይናቅ አዎንታዊ ተጽእኖ ልታሳድር ችላለች ብለን እንድናምን የሚጋብዝ ሚናዋን ስለመጫወቷ የሚያመለክት ሆኖ ይሰማኛል፡፡ ሌላው በዚህ አጋጣሚ መነሳት ያለበት ተያያዥ ነጥብም ደግሞ፤ ኢትዮጵያ የፀጥታ ጥበቃው ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሆና በቆየችበት የአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የተባበሩት መንግስታት በሰሜን ኮሪያ ላይ ተጨማሪ ማዕቀቦች የጣለበትን አስቸኳይ ስብሰባ ያካሄደበት መድረክ መስተዋሉና ስብሰባውን የመሩት በተ.መ.ድ.የኢትዮጵያ ባለሙያ ስልጣን አምባሳደር ዶክተር ተቀዳ ዓለሙ መሆናቸው ነው፡፡

እናም ይህ ሰሞነኛ ዓለም አቀፋዊ ክስተት ኢትዮጵያውያንን ከኮሪያ ልሳነ ምድር ግማሽ ምዕት ዓመት ያለፈው ቀውስ ጋር የሚያቆራኝ የታሪክ ግጥምጥሞሽ የተስተዋለበት ነው ቢባል ከእውነት መራቅ አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም ደግሞ፤ የአሁኑን የኒዩክሌር ጦር መሳሪያ ፍጥጫ ያስከተለ ዘመን ተሻጋሪ መንስኤ ሆኗል ተብሎ የሚታመንበት የሁለቱ ኮሪያዎች ደም አፋሳሽ ጦርነት በተካሔደበት ወቅት፤ ለዓለም ሰላም የቆሙ የመጀመሪያዎቹ የተባበሩት መንግስታት አባል ሀገራት የዛሬዋን ደቡብ ኮሪያ ደግፈው በተሰለፉበት የታሪክ አጋጣሚ ሀገራችን ኢትዮጵያም የራሷን የሰላም አስከባሪ ወታደሮች አዝምታ እንደነበር አይዘነጋምና ነው፡፡

ስለዚህ ከግማሽ ምዕት ዓመት በላይ ተዳፍኖ የቆየው የኮሪያ ልሳነ ምድር የጦርነት እሳት ጊዜ ጠብቆ እየተቀጣጠለ ዓለማችንን ወደፍፁም ጥፋት እንዳይወስዳት በመሰጋቱ ምክንያት፤ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሰሜን ኮሪያ ላይ ማዕቀብ ለመጣል የተገደደበትን ሰሞነኛ መድረክ ኢትዮጵያ በፕሬዚዳንት ልትመራ መቻሏ በእርግጥም ታሪካዊ ግጥምጥሞሽ ነው የሚያሰኝ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡ ለማንኛውም ግን፤ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ጥንትም ሆነ ዛሬ ለመላው የሰው ዘር ዘላቂ ዕጣ ፈንታ ይበጃል የሚሉትን ዓለም አቀፋዊ ሰላም ጨርሶ ከመናጋት አደጋ የሚታደግ ቀና ሃሳብ ደግፈው ቆሙ እንጂ ጎራ ለይተው አንዱን ወገን ለመጉዳት ሲሞክሩ አልተስተዋሉም የሚለው ቁልፍ ነጥብ ላይ ይሰመርበት፡፡ በተረፈ እኔ አብቅቻለሁ፡፡